በቅርብ ቀን የተደረገው ሹም ሽር አማራን ዝቅ አድርጎ እነ ሁሉ ነገር ኬኛን ከፍ ያደረገ ሹመት ነው

በቅርብ ቀን የተደረገው ሹም ሽር አማራን ዝቅ አድርጎ እነ ሁሉ ነገር ኬኛን ከፍ ያደረገ ሹመት ነው። ለመሆኑ በዛሬው ሹመት ስነስርዓት ላይ አቶ ገዱ ለምን ሳይገኙ ቀሩ ብሎ መጠየቅ ተገቢ ይመስለኛል። አቶ ለማ መገርሳን የመከላከያ ሚንስቴር አድርገው የሹሙበት ምክንያት ለሁሉም ግልጽ ይመስለኛል። እሱም የሀገሪቱ ጦር ኃይል ሙሉ ለሙሉ በባለተረኞቹ እጅ እንዲገባና ለወደፊት ከዚያ አቅጣጫ ያልቻለውን ጉብል ወይም ግልብ ስልጣን የሚያሰጋ እንቅስቃሴ ለመጠበቅ ብሎም ለመከላከል ነው። በአጭሩ ጠመንጃውን ከትግሬ ወደ ኦሮሞ ማዛወራቸው ነው። ኢትዮጵያ በአምሮዋቸው የለችም ይሄ ሁሉ ሲሆን። የአቶ ገዱ ሹመት ደግሞ እርሳቸው ከአማራነታቸው በስተቀር ለቦታው እንደማይመጥኑ አውቀው እምቢ ሲሉ ሰጥተናቸው እምቢ አሉ ለማለት ይመስላል። አዎ አማራ ለለውጡ መምጣት እንዲሁም ለእነ ሁሉ ኬኛ ስልጣን መጨበጥ ግንባር ቀደም ሚና እንደመጫወቱና የሀገሪቱ ብዙሃን እንደመሆኑ መጠን የሚገባውን ወሳኝ የስልጣን እርከን እንዳልያዘ ይታወቃል። በእነ ሁሉ ኬኛ ተከዱዋልም።

ታድያ ይህ የአቶ ገዱ ሹመት አማራን ጭጭ ለማሰኘት የተደረገ ይመስላል። መቸም ወያኔዎችና የነሱ አሽከሮች የነኩት ነገር ሁሉ ይረከሳል እንጂ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርንት ቀላል ቦታ አልነበረም። ለዚያም ነው ወያኔዎች የምኒልክ ቤተመንግስትን እስከረገጡበት እላት በውጭ ጉዳይ ሚንስትረነት የሚሾሙት ታላላቅ የሀገራችን ሰዎች የነበሩት። እነ ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ ፣ እነ ዶ/ር ሐዲስ አለማየሁ ፣ እነ ዶ/ር ምናሴ ኃይሌ ፣ እነ ኮ/ል ብርሃኑ ባይህ ፣ እነ አቶ ከተማ ይፍሩ ወዘተ። ታድያ የዶክተሩን ብዛት ስታዩ በሐሰት የሊሾም ነው ወሬ ሲናፈስለትና እውነት ሊሾሙኝ ይሆን ብሎ ልቡ በእንጥልጥል የከረመው ዶ/ር ብርሃኑን ከላይ ከተዘረዘሩት ሰዎች ተርታ እንደማታስገቡ እተማመናለሁ። ከነሱ እኩል ለመታየት የሚያበቃ እውቀትም ሆነ ስብእና የለውም። አቅሙ አይፈቅድም። ከሱስ አቶ ገዱ በመቶ እጥፍ ይሻላሉ። የኔ ጥያቄ ከእርሳቸውስ የሚሻል ሰው ቢቻል ብዙ ቋዋንቋዋ ተናጋሪ ምሁር አዴፓ ውስጥ ጠፍቶ ነውን? አቶ መላኩ ፈንታ ቢሆኑ ይሻል ነበር።

ይህ ሹመት ዶ/ር አብይ ፓርቲውን አዴፓን ሳያማክሩ በግላቸው የወሰኑት የፖለቲካ ወሳኔ ነው። ፖለቲካ ስል ደግሞ አማራን እና አዴፓን በኢትዮጵያ ህዝብ ለማሳጣት ተብሎ የተቀመረ ድርጊት ነው። አቶ ገዱ ለቦታው አልመጥንም ብለው እምቢ ቢሉ አያችሁ ስልጣን የሚገባንን ያህል ለኛ አልተዳረሰም እያሉ ስንሰጣቸው እምቢ ይሉናል ለማለትና ላንድ ለነሱ ሎሌ ለመስጠት ነው። ዶ/ር አብይ አቶ ገዱንም ሆነ አቶ ለማን ሲያጩ ኢትዮጵያንና የሱዋን ክብር እና ሉዋላዊነት ከቁጥር ሳያስገቡ የፖለቲካ ነጥብ አዴፓና አማራ ላይ ለማስቆጠር ብለው ያደረጉት ኃላፊነት የጎደለው ድርጊት ነው። ስለዚህ አዴፓ አስቸኩዋይ ስብሰባ አሁኑኑ አካሂዶ ሌላ በልምድም ፣ በእውቀትም ፣ በቋዋንቋዋ ችሎታም ለቦታው የሚመጥን ተወካይ በአቶ ገዱ ምትክ በእጩነት ለነዶ/ር አብይ ሊያቀርብና እሱን ተመልክቶ ለሕዝቡ መግለጫ ሊሰጥ ይገባዋል።

በላቸው ከዳላስ